አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፸፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ

ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Fourth Year No.79
Addis Ababa July 14, 2016

## ማውጫ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ደንብ ........................................ገፅ ፩

## CONTENTS

The Addis Ababa City Government Rehabilitation Project Office for Displaced Peasants due to Development Regulation………………..Page 1

## ደንብ ቁጥር ? ?/?? ፰

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች በተመለከተ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያስቀመጠ በመሆኑ፤

በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፱ የከተማው አስተዳደር ዓላማ ከተማዋ የሀገሪቱ የንግድና ኢንዱስትሪ ማእከል እንድትሆን የማድረግ እና የአካባቢ ብክለትን በመከላከል የተፈጥሮ ሚዛኑዋን የጠበቀች ጽዱ፣ አረንጓዴና ምቹ ከተማ በማድረግ አመቺ የመኖሪያ የሥራ ሁኔታ የመፍጠር እንዲሁም ነዋሪዎች የከተማውን ሁለገብ እንቅስቃሴ የሚወስኑባትንና የልማት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሃላፊነት እንዳለበት በመደንገጉ፤

## Regulation Number 79/2016

## A Regulation to Provide the Establishment of the Addis Ababa City Government Rehabilitation Project Office for Displaced Peasants due to Development

**Whereas,** various provisions concerning the economic and social affairs of citizens are clearly stated in the Federal Democratic Republic of Ethiopia constitution;

**Whereas**, it is provided under article 9 of the Addis Ababa city charter proclamation number 361/2003 that the objective of the city administration is to enable the city to be the center of trade and industry of the country and protect environmental pollution so as to create a conducive living and working area by making the city clean, green and comfortable through balancing its natural diversity; as well as take responsibility to create a suitable ground for dwellers to decide on various activities of the city and enable them to benefit from its development;

የአዲስ አበባ ከተማ የፌዴራል መንግስቱ ርዕስ ከተማ እና የአፍሪካ ህብረትና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ እንዲሁም የሀገሪቱን ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ጥንቅር የሚያንፀባርቅ ሰፊና አዳጊ ነዋሪ ያለባት በመሆኗ በዘመናዊነቱ ደረጃውን የጠበቀ እና መልካም የሆነ የሥራና የመኖሪያ ከተማ ለማድረግ የሚያስችል ተግባር እየተከናወነባት ያለች ከተማ በመሆኗ፤

ይህን ተከትሎ የከተማዋን እድገት ለማፋጠን ሲባል በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ምክንያት በማስፋፊያ አካባቢዎች ውስጥ የሚኖሩ አርሶ አድሮች ከይዞታቸው እንዲነሱ እየተደረገ የቆየ በመሆኑ እና ወደፊትም ከይዞታቸው የሚነሱ ስለሆነ ከይዞታቸው የተነሱና የሚነሱ ዜጎች ላይ የሚፈጠረውን መፈናቀልና ልዩ ልዩ ችግሮችን በቅድሚያ ለመከላከልና ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ በመሆን የደረሰባቸውንና የሚደርስባቸውን የመልካም አስተዳደር ችግር በመቅረፍ በዘላቂነት ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ መሰረት ለድህነት እና ለተለያዩ ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች እና የህብረተሰብ ክፍሎች ለከፋ ችግር እንዳይጋለጡ መጠበቅ፣ የግለሰቦችን የኑሮ ደረጃ እና የሚያገኙትን ገቢ ማሻሻል፣ ሥራ ለሌላቸው ገቢ የሚያስገኝ ሥራ እንዲያገኙ ማገዝ፣ ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙትም የተሻለ ገቢ ወደ ሚያስገኝላቸው ወይም ምርታማ ወደሆነ ሥራ እንዲሸጋገሩ በማስቻል ገቢያቸው እና ምርታማነታቸው እንዲያድግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዲሁም ለችግር የተጋለጡ ወገኖች የክህሎት ማዳበሪያ ስልጠና እና የማይክሮ ፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻላው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና የአዲስ አበባ ከተማ የአስፈጻሚ አካላትና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፹፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**Whereas,** activities are being carried out in order to make the city civilized, up to the standard and a pleasant place to work and live as the city of Addis Ababa is the capital of the federal government and the seat for the African Union and various international organizations; and having a diversified and growing dwellers that reflect the nation and nationalities of the country and its pluralism;

**Whereas,** following that, it has found necessary to protect peasants who are living in the widening area region, that have been displaced and they would also be displaced, from various problems in advance as a result of their displacement so as to speed up the growth of the city due to the development activity and alleviate their social and economic problems that they have become vulnerable as well as the good governance problems which they have been facing and rehabilitate them in a sustainable manner;

**Whereas,** according to the Ethiopian national social protection policy, it has found necessary to keep individuals, families and communities who are vulnerable to poverty and various natural and man-made problems from worsening problems; improve the living standards of individuals and their income; help the unemployed to have a job that generates income and also enable those who are employed to have a better income or transform them to a productive level so as to create a favorable condition to increase their income and productivity; and enable those compatriots who are vulnerable to a problem to get skill-development training and micro-finance support in order to create a market link;

**Now, therefore,** in accordance with article 23/1/ (f) of the Addis Ababa city government revised charter proclamation number 361/2003 and article 84 of the Addis Ababa city government executive and municipal service organs re-establishment proclamation number 35/2012, the Addis Ababa city government cabinet has issued this regulation as follows.

፰ in the future through scrutinizing their experience and ensure they benefit from it;

፫. በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ አርሶ አደሮች የተከፈላቸውን ካሳ በዘላቂነት መጠቀም እንዲችሉ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የኑሮ ሁኔታቸው እንዲሻሻል ማድረግ፤

፬. የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች ከይዞታቸው ከመነሳታቸው በፊት በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ እንዲችሉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት፤

፭. ቀደም ሲል በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ተነስተው ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ አርሶ አደሮችን ተገቢ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት በመልሶ ማቋቋም ኑሯቸው እንዲሻሻል ማድረግ፤

፮. በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ አርሶ አደሮች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እሴቶቻቸው በሚያስቀጥል መልኩ እና መሰረተ ልማት በተሟላበት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

፯. በማስፋፊያ አካባቢ ነዋሪ የሆኑ አርሶ አደሮች በልማት ምክንያት እንዲነሱ ሲደረግ በህጉ መሰረት ተገቢውን የካሳ ክፍያና ምትክ ቦታ ማግኘታቸውን መከታተልና ከሚመለከታቸው ጋር ተቀናጅቶ መሥራት፡፡

?. ??????

፩. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

ሀ. የስራ አመራር ቦርድ

ለ. ዋና ሥራ አስኪያጅ

ሐ. ምክትል ስራ አስኪያጅ

መ. ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፪. እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሊኖሩት ይችላል፡፡

፫. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ተጠሪነት ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ይሆናል፡፡

3. Draft projects for the peasants who are displaced due to development so as to enable them to use their compensation payment in a sustainable way so as to improve their living condition;
4. Work in coordination with the concerned bodies to aware the peasants who are displaced due to development to have enough preparation before their displacement from their premises;
5. Collect and organize information about those peasants who are exposed to various social and economic problems due to development displacement from their property in the past so as to rehabilitate their lives;
6. Create a favorable condition for peasants who are displaced because of development in order to rehabilitate them in a way to continue their social, economic and cultural values and in areas where infrastructures are fulfilled;
7. Follow up whether those peasants who are displaced due to development from widening area get the relevant compensation and substitute land according to the law and work in coordination with the concerning bodies.

**7. Organization**

1. The office of the project shall have the following organization:
   a. Management board;
   b. General Manager;
   c. Deputy managers;

6. Ensure that peasants who are displaced due to development get a fertile land when a substitute land is given and enable them to benefit from the social and economic services;
7. Strive for the social values, cultural ties, language and other related rights of the peasants who are displaced due to development to be respected accordingly; perform in coordination with the concerned bodies;

፯

፲፫. ከሚያገኙት ገቢ የቁጠባ ባህላቸው እንዲሻሻልና እንዲዳብር የሚያስችሉ ተግባራትን ይቀይሳል፣ ያስፈፅማል፤

፲፬. ሌሎች ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን ያከናውናል፡፡

?. ?? ??? ?? ?? ? ? ????? ????? ?????

ዋና ሥራ አስኪያጁ በከንቲባው የሚሾምና ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በዚህ ደንብ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት የጽህፈት ቤቱን ስራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

፰. የአርሶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚያስችሉ አዳዲስ ኘሮጀክቶችን ይቀርፃል፣ ሃሳቦችና አሰራሮችን ይነድፋል፣ ይቀይሳል ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፱. በልማት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተነሱ አርሶ አደሮችን አዋጭ በሆነ የሥራ እድል ፈጠራ ፕሮግራሞች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያቅዳል፣ ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፤

፲. ለዓላማው መሳካት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ከሚችሉ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመመስረት የቴክኒክና የሙያ እገዛዎችን በማፈላለግ አርሶ አደሮቹ መጠቀም የሚችሉበትን መንገድ ይቀይሳል፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፩. ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮችና የአርሶ አደር ቤተሰቦች እንደየችሎታቸውና እድሜያቸው አስፈላጊውን የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣ በተሰጣቸው የክህሎት ሥልጠና መሠረት በአካባቢው በሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ቅድሚያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲፪. በልማት ምክንያት የሚነሱ አርሶ አደሮች የተሰጣቸውን ካሳ አቀናጅተው ወደ ተሻለ ልማት (የኢንቨስትመንት አማራጮች) የሚገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይደግፋል ፤ይከታተላል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

8. Create new projects that enable to improve the livelihood of peasants; draft proposals and procedures; directs and implement it when it is allowed;
9. Plan, follow-up and implement so as to participate peasants who are displaced from their living area due to development in an advantageous job-creation programs and make them beneficiaries;
10. Create a relationship with institutions that shall help the meeting of its goal in order to find technical and vocational support which make the peasants beneficial; implement it when it is allowed;
11. Ensure that the displaced peasants due to development and their families get the necessary skill training according to their abilities and age; enable them to get priority and benefit from the job opportunities created in the area based on the skill training they had received;
12. Facilitate, support and follow up conditions for the displaced peasants due to development to use their compensation payment together and enter

into a better development and investment options; the detail shall be specified through a directive;

13. Design and Carry out activities to improve and develop their saving habit;

14. Perform other activities related with the objectives of the project office.

**9. Power and Duties of the General Manager of the Office**

The general manager shall be appointed by the mayor and accountable to the bureau head having the following power and duties:

1. Control, administer and run the activities of the office in accordance with the power and duties given by this regulation;

፰

፯. ለፕሮጀክቱ ስኬት አስፈላጊ ከሆኑ አካላት ጋር ግንኙነትና ስምምነት በማድረግ የስራና የልምድ ልውውጥ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለቦርዱ እና ለቢሮው ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፰. ለፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ በተመደበ በጀትና የስራ እቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

፱. የጽህፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርድ፣ ለቢሮው እና ለሚመለከተው አካላት ያቀርባል፤

፲. ሥራ አስኪያጁ ለጽህፈት ቤቱ የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ወይም በሙሉ ለምክትል ሥራ አስኪያጁ በውክልና መስጠት ይችላል፤

፪. የጽህፈት ቤቱን የአደረጃጀት መዋቅርና የሰው ሀይል ፍላጎት፣ ደመዎዝና አበል እያዘጋጀ ለቦርድ በማቅረብ ያስፀድቃል፣ በፀደቀው መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፫. በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት ለጽሕፈት ቤቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፬. የፕሮጀክቱን ጽሕፈት ቤት ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀትና የስራ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለቦርዱ እና ለቢሮው ያቀርባል፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭. የወሩን፣ የሩብ፣ የመንፈቅ እና ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም እንዲሁም ሌሎች ሪፖርቶችን ለቦርዱ፣ ለቢሮው እና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤

፮. ከሦስተኛ ወገን ጋር የሚደረግ ግንኙነት ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፣ አግባብ ካላቸው ተቋማት ጋር በአጋርነት ለመሥራት የሚያስችሉ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2. Cause the approval of the organizational structure, human resource need, salary and allowance of the office after its preparation and submission to the board;

3. Employ, administer and sack necessary employees for the office according to government employees administration law;

4. Prepare the annual plan, budget and work program of the office of the project and submit it to the board and bureau; implement it when it is allowed;

5. Submit monthly, quarterly, semi-annual and annual work performance and other reports to the board, bureau and other concerned bodies;

6. Represent the office in all relations with a third party; review and implement systems that

1. Carry out the preparation of plan and performance report of the office by supporting the general manager so as to make it ready;
2. Perform activities particularly delegated to him in the absence of the general manager or in time of his inability to carry out the work;
3. Perform activities in accordance with the designation of the general manager;
4. Carry out other activities assigned by the general manager.

## Part Three
## Organization, Power and Duty of the Board

**11. Organization of the Board**

1. A board of directors that administer and control the office of the project shall be established by this regulation having 9-11 members;
2. The chairpersons, deputy chairperson and members of the board shall be appointed by the mayor;
3. The board shall be accountable to the mayor;

፩. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን የአሰራርና የህግ ማዕቀፎች ተጠንተው ሲቀርቡለት መርምሮ ያጸድቃል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

ሀ. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን መዋቅርና ደመወዝ ስኬል፣ እንዲሁም የመንግስት ሠራተኞች ህግ መሰረታዊ ዓላማዎችን በመከተል የተዘጋጀ ሠራተኞች የሚተዳደሩበት መመሪያ ያወጣል፤

ለ. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን የማቋቋሚያ ገንዘብ አከፋፈልና አጠቃቀም የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤

፫. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ ዕቅድ መርምሮ ያጸድቃል፣ እንዲሁም በከተማው አስተዳደር ለጽህፈት ቤቱ የተፈቀደለትን ዓመታዊ በጀት ተዘርዝሮ ሲቀርብለት አይቶ ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

፬. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ አፈፃፀም በእቅዱ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ስለአሰራሩም ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፤

፭. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም በቦርዱ አባላት ፪/፫ኛ ድምፅ በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

፲

፬. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ አባልና ፀሀፊ ይሆናል፤

፭. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከንቲባው ሌሎች ተጨማሪ የቦርድ አባላትን ሊሰይም ይችላል፡፡

**፲፪. ???? ????? ????**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

4. The general manager of the office of the project shall be a secretary and member of the board;
5. If it has found necessary, the mayor may appoint other additional board members.

**12. Power and Duty of the Board**

The board shall have the following power and duties:

1. Scrutinize and approve procedures and legal frameworks of the office of the project when they are submitted after a study;
2. Without prejudice to sub-article 1 of this article, the board:
   a. Issue directives about the structure and salary scale of the office of the project and for the administration of employees based on the basic objectives of government civil-servant laws;
   b. Issue directives concerning the payment and utilization of the establishment money of the office of the project;
3. Scrutinize and approve the annual plan of the project office; and scrutinize the detailed allocated budget of the project office and deliver it to the concerned body;
4. The board shall ensure whether the performance of the office of the project has been carried out according to its plan; give support for its implementation;
5. The board shall have its ordinary meeting once in a month; provided, however, that it may hold extraordinary meetings at any time as may be necessary if the chairperson or 2/3rd of the vote of the board members calls for it;



፲፫. ???? ?? ???? ? ?

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤታዊ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፰/፪ሺ፬ የተደነገገው ሥልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ ከተግባሩ ጋር ግንኙነት ስለሚኖራቸው ባለድርሻ አካላት ሚና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣው መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

??? ???

?? ?? ??????

??. ???

የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የበጀት ምንጭ የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩. በከተማው አስተዳደር ከሚመደብ በጀት፤
፪. ከለጋሽ ድርጅቶች ከሚገኝ ድጋፍና እርዳታ፡፡

??. ???? ? ???? ????

፩. ጽህፈት ቤቱ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሠረት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤
፪. የጽህፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና የገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና ኦዲተር፣ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና በቢሮው የውስጥ ኦዲተር ሊመረመር ይችላል፡፡

፮. በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተነሱ አርሶ አደሮች ስለሚቋቋሙበት አጠቃላይ ሁኔታ እገዛ የሚያደርግ አካላት ተግባሩን በአግባቡ እየፈጸሙ መሆኑን ያረጋግጣል፣ይደግፋል፡፡

6. Make sure and support whether those bodies, who provide support about the general conditions for the rehabilitation of peasants who

**16. Inapplicable Laws**

Any regulation, directive or customary practice, which is in consistent with this regulation, shall not be applicable on matters covered under this regulation.

**17. Duty to Cooperate**

Any person shall have the duty to cooperate in the implementation of this regulation.

**18. Duration for the Office of the Project**

The duration for the office of the project shall be five years. However, it may be prolonged based on examining its implementation of activities and meeting the goals according to the decision of the cabinet of the city government.

**19. Issuing Directives**

The bureau may issue directives for the implementation of this regulation.

**20. Amending the Regulation**

The cabinet of the city government may amend this regulation, if it is believed necessary.

**21. Effective Date**

This regulation shall enter into force as the 14th day of July 2016.

**Done at Addis Ababa**

**This day of July 14, 2016**

**Diriba Kuma**

**Mayor of Addis Ababa City**